# ስኬታማ ውይይት (ሙግት) ስለማድረግ

ከ ዶ/ር ተስፋዬ ሮበሌ አገልግሎትና ትምህርት ላይ የተመሰረተ

በ አሌክስ እና በ ማህሌት ተዘጋጀ

ሰሜን አሜሪካ፣ ጃንዋሪ 2026

# ማውጫ

- ትዝብታችን
- ስለተሚጋቾቻችን ማወቅ የሚጠቅሙን ቁልፍ ጉዳዮች
    - አስተምህሮዎቻቸውን
    - ቅደመ እሳቤአያቸውን (መቅድመልባዊያቸውን)
    - እኛ በነሱ አእምሮ ውስጥ ያለን ስዕል
- የሙግት ጥበብና አተገባባር ( የ ሙግት አወቃቀር፣ አደረጃጀትና አሰናዘር ከሚለው የ ዶ/ር ተስፋዬ ሮበሌ ትምህርትና አገልግሎት የተወሰድ)
- የ ማስረዳት ግዴታን ( ሃላፊነትን) ወደ ተሚጋቾችን ማዞር፡ ( ከ ዶ/ር ተስፋዬ ሮበሌ ጽሁፍ የተወሰደ)
- ምክርና ማጠቃለያ

# ትዝብታችን

- በተከታታይ በተሳትፍንባቸው የሙግት/ የክርክር መድረኮች የታዘብናቸው ማሳተካካያ ስራ የሚያስፈልጋቸው ነጥቦች
  - ተሟጋቾችን ማስጨነቅ፣ ሲናገሩ ማቋረጥ፣ መልሳቸውን ዲክቴት ለማድረግ መሞከር፣ “ምን ብዬ ልመልስህ” ብለው እስኪጠይቁ ድረስ ማጣደፍ፣ ማካለብ
  - አንድ ብቻ ተሟጋች መሆኑን መርሳትና የተቀሩት በሙሉ በአንዱ ተሟጋች ላይ በመረባረብ ውይይቱን ጥሎ እስኪሄድ ድረስ ማስጨነቅ
  - በሰዓት አለመገደብና ሳይጨርሱ ማቋረጥ፣ ደጋግሞ ማቋረጥ፣ ማቆራረጥ፣ ማበሳጨትና መድረኩን ጥለው እንዲሄዱ ማድረግ ከዛ የተሟጋች ያለህ ብሎ መጣራት እንደጋን ያንኑ ስህተት ደግሞ መስራት…
  - አስተምህሮአቸውን በሚገባ አለማወቅና በውይይት መደረክ ላይ አስተምህሮአቸውን ደጋግሞ መጠየቅ
  - የንቀት፣ አልፎ አልፎም የስድብ ቃላትን መወርወር፣

## ስለተሚጋቾቻችን ማወቅ የሚጠቅሙን ቁልፍ ጉዳዮች

- ቅደም እሳቤ ወይም መቅድመ ልባዊ፡ የሰው ልጅ ወና ቤት አይደለም፣ ሁላችንም በሁሉም ጉዳይ በተለይ ደግሞ በሃይማኖት ጉዳይ ከተለያየ ምንጭ የገበየነው ቅድመ እሳቤ አለን፤ ተሚጋቾቻንም አላቸው። ያን ቅድመ እሳቤ ማወቅ ፣ መረዳትና ማክበር ያስፈልገናል
- አስተምህሮ፣ የታወቀው የዕቅበተ እምነት ምሁር ዋልተር ማርቲን እንዳለው የተሚጋቾቻንን አስተምህሮ በራሳችን አስቀድመን ማጥናት አለብን እንጂ በውይይት መድረክ ላይ ለመማር ለማወቅ ማሰብ የለብንም. አስቀድመን ማወቃችንን የክርክር የበላይነትን እንድንይዝ ይረዳናል።
- እኛ ተሚጋቾቻንን ስተዋል ብለን እንደምናስብ እነርሱም እኛን ስተዋል፣ ወደ እውነት ሊመልሱን ነው የሚመጡት፤ በሙግታችን ቢረቱ እንኳን በመድረክ ላይ እጅ አይሰጡም። ለምሳሌ እኛን ባለ 3 አምላክ ተከታዮች አርገው ይስሉናል፣ ያዝኑልናል።

# የሙግት ጥበብና አተገባባር

- ሙግት ላይ አንድ መጠየቅ ያለብን.....የትኛውን የእውቀት ክፍል ነው challenge እያደረኩ ያለሁት የሚለውን ነው።

- አንድ ሰው እውቀት አለው የምንለው እነዚህን 3 ነገሮች ሲያሟላ ነው። This is “Model of knowledge” by the famous Greek philosopher Plato...

  1. እውነትን ሲያውቅ (the truth that exists, the reality )
  2. ያንን እውነት ሲያምን
  3. ለሚያምነው እውነት በቂ ማስረጃ ሲኖረው ነው

- ሙግት ከሚዋቀርባቸው መንገዶች ወሳኞቹ ሁለት መንገዶች ፤ ከትካች አጸፋ እና ተቃራኒ አጸፋ ናቸው።

- ከትካች አጸፋ ተሟጋቾቻችን ይዘው የመጡት ጥቅስ ላይ ብቻ ተወስነን ክፍሉ የነሱን የስህተት አስትምህሮ የሚደግፍ አለመሆኑን ይልቁንም ሌላ መልዕክት/ አንድምታ ያለው መሆኑን የማስረዳት ብቃት ነው። ለምሳሌ ኢሳ 9:6

Ø ከትካች አጸፋ → Justification/ ምክንያትን ያፈርሳል
Ø If justification fails, knowledge fails
Ø መሰረታቸው ጠንካራ እንዳልሆነ ያሳያል

## ......የሙግት ጥበብና አተገባባር

- ተቃራኒ አጸፋ ደግሞ ተማጓቻችን አንድ ጥቅስ ይዞ ሲመጣ እኛ ደግሞ ያመጣውን ጥቅስ የሚቃረን ሌላ ጥቅስ ይዘን በመምጣት የምናስቆምበት/ የምንጠይቅበት ዘዴ ነው።
- በሙግት ወቅት ሁለቱንም እያሰባጠርን በተለይ ደግሞ የተቃራኒ አጸፋ ጥያቄዎች ላይ ማተኮሩ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ብዙ የመናገር እድል ስንሰጣቸው ብዙ የመጠየቅ እድል እናገኛልን።
- ጥሩ ተሟጋች ለማሸነፍ ሳይሆን መሞከር ያለበት የሚሟገተውን ሰው የእውቀት መዋቅር ( structure) ነው ማወቅ ያለበት። ሰውየውን በማስወራት ማለት ነው።

# የ ማስረዳት ግዴታን ( ሃላፊነትን) ወደ ተሚጋቾችን ማዞር

- ሰዎች በባህርያቸው ብዙ መናገር፣ ማስረዳትን ይወዳሉ፣ ይህንን ሁኔታ ተሚጋቾቻን ያላቸውን ሁሉ እንዲያወጡ ልንጠቀምበት እንችላለን።
- ዋነኞቹ የኑፋቄ ትምህርቶች መጽሃፍ ቅዱስን የመተርጎም ስልጣን አለን ብለው አያምኑም፤ ስለዚህ ስንናገር አይሰሙንም ይልቁንም ስንጠይቃቸው ሊያብራሩልን ይወዳሉ ፤ ያንግዜ እኛ ደሞ በርካታ አጋላጭ ጥያቄዎችን አዘጋጅተን እንዲጋለጡ እናደርጋለን።
- ለምሳሌ ሥላሴን አስረዱን ሲሉን የለም እናንት ወልድና አብ አንድ ናቸው የሚለውን አስረዱን እንበላቸው።

# ምክርና ማጠቃለያ

- በተማጋጀቻችን አስትምህሮ ላይ በቂ ግንዛቤ ይኑረን፤ እምነታችሁ እንደሚለው እንበል እንጂ እምነታችሁን ንገሩን አንበል።
- ብዙ ለመጠየቅ እንዘጋጅ፣ ብዙ ለማውራት እንሞክር። እነርሱ በጣም ጥቂት ናቸው እኛ ብዙ ነን፣ ተናጋሪያቸው ጨርሻለው ሲሉ ብቻ እኛ እንቀጥል።
- በርካታ ጥያቄዎችን እናዘጋጅ፣ አንድ በ አንድ እንጠይቅ አስፈላጊ ሲሆን ከትካች አጸፋ እንጠቀም፣ ሲያስፈልግ ተቃራኒ አጸፋ እንሰንግበት።
- ለ አንድ ተናጋሪ የተወሰን ግዜ ይሰጠው፣ ከዛ ለጠያቂ ከዛ ለተናጋሪ፣ ንግግርን አናቋርጥ፤ አመስግነን እንሸኝ፤ ደግመው እንዲመጡ እናርጋቸው።
- ተማጋቶች በመድረክ ላይ ይሟገታሉ እንጂ እንዲያምኑ አይጠበቅም።

# ምክርና ማጠቃለያ

ሙግትን መርታት የሙግት አንዱ ዐላማ ቢሆንም፣ ተሟጋቹ የምንሟገትለትን እውነት ገንዘቡ ያደርገው (ይቀበለው) ዘንድ ግለሰቡን መርዳት ሌላው ሙግት ዐላማ ነው:: በአቀራረብ ሕጸጽ (ሥነ ምግባራዊ እንከን) ግለሰቡ ሙግቱን አድምጦ እውነታውን ላለመቀበል ልቡን ካደነደነ፣ ጥረታችን በግማሽ ከሽፏል:: ስለዚህ ሙግትን ማሸነፍና ተሟጋቹን ላስተላለፍነው እውነት ማሸነፍ፣ እጅግ የተለያዩ ጉዳዮች እንደ ሆኑ ሊጠፉን አይገባም::

ዶ/ር ተስፋዬ ሮበሌ-ሥነ አመክንዮ ገፅ 66

- ክርስቲያናዊ ክርክር ዓላማው መሸነፍ ወይም የሌላን ሽንፈት ማሳየት አይደለም፤ እውነትን በትህትና መግለጥ ነው።
- ሙግት ምንም ያህል በአግባቡ ቢካሄድም እንኳን እውነትን በግድ ሰው ጭንቅላት ውስጥ መክተት አይቻልም ነገር ግን ለማሰብና ለማንቃት እድል ይከፍታል።